# የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጪ ዜጎች በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ

# የማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 18 /2006

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Foreign Affairs

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

## መግቢያ

የኢፌድሪ መንግስት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ሀገር ዜጐች ከትውልድ ሀገራወቸው ጋር ትስስር ኖሮአቸው በአገራቸው ልማት ተሳታፊ በመሆን አገራቸውን ጠቅመው ተጠቃሚ መሆን እንዲችሉ በአገር ውስጥ አመቺ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ አዋጅ ቁጥር 270/94፣ አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንብ ቁጥር 2252/2003 ደንብ ቁጥር 101/2004 እንዲሁም ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የማስፈፀሚያ መመሪያች ወጥተው ለተወላጁ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ አገልግሎት በሀገር ውስጥ በኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ እና በውጪ ሀገር በኢፌድሪ ሚሲዮኖች ሲሰጥ እንደነበር ይታወቃል፡፡

በዚህ መሠረት አያሌ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ አገልግሎት አግኝተው በሀገራቸው ልማት እየተሳተፉ የሚገኙ ሲሆን በአገር ቤት ቆይታቸው ወቅትም ህጉ በሰጣቸው መብቶች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ተወላጁ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በየጊዜው የተለያዩ ጥያቄዎች ለማንሳት ቅሬታ እያሰማ በመሆኑ፣ የእስከአሁኑ አሰራር የህጉን አላማ ለማስፈጸም ባለማስቻሉ እና ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች መመሪያውን በዚህ መንፈስ በማሻሻል መፍታት አስፈልጓል፡፡

1. **መመሪያውን ማሻሻል ያስፈለገበት አብይ ምክንያቶች**
   - በሀገር ውስጥና በውጭ አገር በመታወቂያ አገለግሎት አሰጣጥ ረገድ የነበረው አሠራር ወጥነት የሌለው መሆን፣
   - ከሚሲዮን ሚሲዩን በመታወቂያ አገልግሎት አሰጣጥ የነበረው አፈፃፀም የተለያየና አንዳንድ ጊዜ በሚሲዩን መሪያዎችና አገልግሎቱን በሚሰጠው ዲፕሎማት መልካም ፈቃድ ላይ የተመሠረተ መሆን፣
   - አገልግሎቱን ለመስጠት በመመሪያው የተቀመጡት አንዳንድ መሥፈርቶች በተለይ በማስረጃ አቀራረብ በተጨባጭ ሲታይ ሊተገበሩ የማይችሉ ሆነው መገኘት፣
   - በመታወቂያ ካርድ አሰጣጥ የተጠያቂነት አሠራር አለመኖር፣

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs

- ኢትዮጵያ ውስጥ ረዘም ላሉ ዓመታት ኖረው በነበራቸው አስተዋጽኦ በመኖራቸው በአዋጅ ቁጥር 270/94 ለውጭ አገር ዜጐች በልዩ ሁኔታ የሚሰጠው የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ለኢትዮጵያ ተወላጆች ከሚሰጠው የመታወቂያ ካርድ አገልግሎት ጋር በአንድነት የሚስተናገድበት ሁኔታ በመኖሩ ይህንን ለጊዜው አቆይቶ ወደፊት ማየት በማስፈለጉ፣
- የመታወቂያ ካርድ አገልግሎት አሰጣጥ የአዋጁን ዓላማና መንፈስ ማእከል ባደረገ መልኩ እተፈፀመ አለመሆኑ፣
- በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር አገልግሎቱ ሲሰጥ የሚሞላው የማመልከቻ ቅፅ በተሟላ መልኩ የማይሞላ በመሆኑ ለአገልግሎት አሰጣጥ አስቸጋሪ የነበረ መሆኑ፣
- መታወቂያው ከዜግነት በመለስ ለተጠቃሚው በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት ሆኖ ሳለ ትኩረት ሰጥቶ በጥንቃቄ የማይከናወን መሆኑ፣

## 2. የመመሪያው መርሆዎች

- ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ወጥ፣ ግልፅና ፍትሃዊ የሆነ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ አገልግሎት መስጠት፣
- ደረጃውን የጠበቀና security feature ያለው የተወላጅነት መታወቂያ ካርድ አገልግሎት በማእከል መስጠት መቻሉ፣
- አገልግሎት ተቀባዩ በአገልግሎት አሰጣጡ ያለውን ቅሬታ የተዘረጋውን የአሠራር ስርአት ተከትሎ እንዲያቀርብ ማድረግ፣
- የተወላጅነት መታወቂያ ካርድ አገልግሎት አሰጣጥ በአዋጁ፣ በደንቡና ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው በዚህ መመሪያ መሠረት ማከናወን፣
- የአገልግሎት ጠያቂው የሚሰጠውን የተወላጅነት መታወቂያ ካርድ መረጃ በዘመናዊ መንገድ አደራጅቶ በመያዝ ለተፈለገው አገልግሎት እንዲውል ማድረግ፣

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሪከርድ ክፍል Records Section Ministry of Foreign Affairs

## 3. የመመሪያው አፈፃፀም

- የመታወቂያው ባለቤት መታወቂያው የሚያስገኘውን ጥቅም ለማግኘት የፀና መታወቂያ ካርዱን መያዝ ይኖርበታል፡፡

- የተወላጅ መታወቂያ ካርዱ ሲታደስ፣ ሲሰረዝ፣ ሲታረም፣ ሲተካ እና ሲመለስ በዚህ መመሪያ በተመለከተው አግባብ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

- መመሪያው በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ተዘጋጅቶ ለፈፃሚ አካላት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

- መመሪያው ተፈፃሚ ከመሆኑ በፊት በሀገር ውስጥ የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ እና በውጭ ሀገር የኢፌድሪ ሚሲዮኖች ለየተቋማቸው ባልደረቦች በመመሪያው ዓላማ፣ መንፈስና ዝርዝር አፈፃፀም ላይ ገለፃ መስጠት፣ በየተቋማቱ የውስጥ ማስታወቂያ ሠሌዳ እና ድረ-ገጾች እንዲሁም በመለጠፍና ለባለድርሻ አካላት አመቺ የሆነውን መንገድ በመጠቀም በመመሪያው ላይ የተሟላ ግንዛቤ መፍጠር ይገባል፡፡

- ከመመሪያው ዓላማና መንፈስ ውጪ መፈፀም አግባብ ባለ ሕግ መሠረት ተጠያቂነት ስላለው በየደረጃው ያሉ ፈፃሚ አካላት በመመሪያው መሠረት ተገቢውን አገልግሎት የመስጠት እና አገልግሎት ጠያቂውም በመመሪያው በተመለከተው አግባብ መብቱን ማስከበርና ግዴታውን መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡

- የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ እና የኢፍድሪ ሚስዮኖች መመሪያውን ለሚያስፈፅሙ አካላት የሥራ ዝርዝር በመስጠት የመመሪያውን መልካም አፈፃፀም መከታተል ይገባቸዋል፡፡

- በመመሪያው አፈፃፀም የሚታዩ ጉልህ ችግሮች ሲያጋጥሙ ጥያቄው ይህንኑ ለማስፈፀም በዚህ መመሪያ ለተቋቋመው የጋራ ኮሚቴ ቀርቦ ኮሚቴው ለሁለቱ ተቋማት የበላይ አመራር የውሳኔ ሃሳብ በማቅረብ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs

በአጠቃላይ መመሪያው ቀደም ሲል የነበረውን የተዘበራረቀ፣ ግልፅነት እና ፍትሃዊነት የጐደለው አሠራር በማስተካከል ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለኢትዮጵያ ተወላጅ ለመስጠት ታስቦ የወጣ በመሆኑ አስፈጻሚ አካላት እና አገልግሎት ጠያቂው ለመመሪያው ተፈፃሚነት የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ ተገቢውን መፈፀም ይገባቸዋል፡፡

## የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣውን አዋጅና ደንብ ለማስፈጸም ግንቦት 1 ቀን 1994 የወጣውን መመሪያ ለማሻሻል የወጣ «የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ» አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 18/2006 ዓ.ም፣

የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ለመስጠት ቀደም ሲል ሲሰራበት በነበረው መመሪያ የተጠቀሱት መስፈርቶች የአገራችን መረጃ አያያዝ ዘመናዊ ባለመሆኑ ከአገራቸው ከወጡ ረዘም ያለ ጊዜያት ያስቆጠሩ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በመመሪያው የተመለከቱ ማስረጃዎችን ማቅረብ ባለመቻላቸው የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት መመሪያውን ማሻሻል በማስፈለጉ፣

ከዚህ በፊት ባልተደራጀ መልኩ ይሰራባቸው የነበሩ መመሪያዎችን በአንድነት በማዘጋጀት ግልፅ የሆነ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣ በመመሪያው የተመለከቱ አሠራሮች በአዋጅ ቁጥር 270/94 እና ደንብ ቁጥር 101/96 መንፈስ ጋር ተጣጥመው እንዲሄዱ ማድረግ እንደሚያስፈልግ በመገንዘብ፣

በአዋጅ ቁጥር 270/94 አንቀጽ 17/2 መሠረት የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ አሰጣጥን ለማስፈፀም ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 18/2006 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣

   2.1. 'ሚኒስቴር' ማለት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማለት ነው።

   2.2. 'አገልግሎት' ማለት የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት መ/ቤት ማለት ነው፡

   2.3. 'ሚሲዮን' ማለት በውጭ ሀገር የሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ወይም ቋሚ መልእክተኛ ጽ/ቤት ወይም ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት ማለት ነው፤

   2.4. 'ኢሚግሬሽን' ማለት የኢሚግሬሽን እና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ማለት ነው።

   2.5. 'የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ' ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ ለሆነ የውጭ ሀገር ዜጋ የሚሰጥ መታወቂያ ካርድ ማለት ነው።

   2.6. 'የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የዉጭ ሀገር ዜጋ የትዳር ጓደኛ የመታወቂያ ካርድ' ማለት የኢትዮጵያ ተወላጅ መሆኑን የሚገልፅ መታወቂያ ካርድ የተቀበለ የዉጭ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
Ministry of Foreign Affairs
ሪከርድ ክፍል
Records Section

ሀገር ዜግነት ያለው የትዳር ጓደኛ መሆኑን የሚገልጽ የመታወቂያ ካርድ ማለት ነዉ፡፡

2.7. የበላይ አመራር በሚኒስቴሩ ሚኒስትሩና ሚኒስትር ዴኤታዎች እንዲሁም በአገልግሎቱ ዋና ስራ አስኪያጅና ምክትል ሥራ አስኪያጆች ናቸው፡፡

2.8. 'የጋራ የቴክኒክ ኮሚቴ' ማለት ከትውልድ ኢትዮጵያ መታወቂያ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ጉዳዮችን በተመለከተ የውሳኔ ሀሳብ ለበላይ አመራር የሚያቀርብ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ተውጣጥቶ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፡፡

2.9. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትን ፆታ ያካትታል፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ በተሰጣቸውና በሚሰጣቸው የውጭ ዜጐች ሁሉ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

4. <u>የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ አሠጣጥ</u>

የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እንዲሰጠው ያመለከተ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ፡-

4.1 መታወቂያውን ለማግኘት ዜግነት ከወሰደበትን አገር የተሠጠው አገልግሎቱ የፀና ፓስፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

4.2 ከላይ በተራ ቁ. 4.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሚከተሉት አንዱን በተጨማሪ ማቅረብ አለበት፡፡

4.2.1 የአመልካቹ አግባብ ካለው አካል የተረጋገጠ የልደት ምስክር ወረቀት ማስረጃ ቅጂ፣ ወይም

4.2.2 ያአመልካቹ የቀድሞ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ቅጂ፣ ወይም

4.2.3 የወላጅ (አባት/እናት) ፓስፖርት ወይንም የኢትዮጵያ ነዋሪነት መታወቂያ ካርድ ቅጅ፣ ወይም

4.2.4 አግባብ ካለው አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የወላጆቻቸው የወራሽነት ማስረጃ ቅጅ፣ ወይም

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሪከርድ ክፍል Records Section Ministry of Foreign Affairs

4.2.5 ስልጣን ካለው ፍ/ቤት የተሰጠና አግባብ ባለው አካል ተረጋግጦ የቀረበ የጉዲፈቻ ማስረጃ ቅጂ፣ ወይም

4.2.6 ሥልጣን ካለው ፍ/ቤት የተሰጠና አግባብ ባለው አካል ተረጋግጦ የቀረበ የተወላጅነት ማረጋገጫ ማስረጃ ቅጂ፣ ወይም

4.2.7 የቅርብ ቤተሰብ /ወንድም፣ እህት፣ በሌሎች ሦስት ኢትዮጵያውያን/ ትውልደ ኢትዮጵያውያን/ ስለመሆኑ እንደአስፈላጊነቱ በአካል ቀርበው በሚሰጥ ምስክርነት ማረጋገጫ፣

4.3 መታወቂያውን ለማግኘት የሚያስፈልገውን የጣት አሻራ በሚሲዮን ጽ/ቤት ወይም በአካባቢው በሚገኝ ፖሊስ በኩል ተጣርቶ በሚቀርብ አሻራ /የኢትዮጵያ ፓስፖርት ጥያቄ በሚስተናገድበት ሁኔታ/ ወይም በኢሚግሬሽን ጽ/ቤት መስጠት አለበት፣

4.4 ከላይ በተራ ቁጥር 4.1 እንዲሁም ከተራ ቁጥር 4.2.1 እስከ 4.2.7 ከተመለከቱት አንዱን አሟልቶ

4.4.1 ሁለት በቅርብ ጊዜ የተነሳ ሙሉ ፊት የሚያሳይ ለፓስፖርት በሚሰጠው ልክ የሆነ ፎቶግራፍ እና

4.4.2 ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት፣

በሀገር ውስጥ ሲሆን ለኢሚግሬሽን ከኢትዮጵያ ውጭ ሲሆን በሚኖሩበት ሀገር ለሚገኘው /ለተወከለው/ የኢፌዲሪ ሚሲዮን ማቅረብ ይኖርበታል።

## 5 <u>አካለ መጠን ላልደረሱ የኢትዮጵያ ተወላጅ ልጆች ስለሚሰጥ አገልግሎት</u>

5.1 አካለ መጠን ያልደረሱ የኢትዮጵያ ተወላጅ ልጆች ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር በወላጅ አማካይነት መታወቂያ ለመውሰድ

5.1.1 የልጁ/የልጇን ሕጋዊ የልደት የምስክር ወረቀት፣

5.1.2 አገልግሎቱ የጸና ፓስፖርት፣

5.1.3 የወላጁ/ጂ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እና

5.1.4 ልጁ /ልጅቷ በቅርብ ጊዜ የተነሳው/ችው ሙሉ ፊትን የሚያሳይ ሁለት ጉርድ ፎቶግራፍ ከማመልከቻ ቅጽ ጋር በማያያዝ

በአገር ውስጥ ሲሆን ለኢሚግሬሽን ከኢትዮጵያ ውጭ ሲሆን በሚኖርበት ሀገር ለተወከለው የኢፌዲሪ ሚሲዮን ማቅረብ ይኖርበታል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs

5.2 ለአካለ መጠን ያልደረሱ የኢትዮጵያ ተወላጅ ልጆች ከላይ በተራ ቁጥር 5.1 የተመለከተውን አሟልተው የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የአገልግሎት ክፍያውን ፈጽሞ እንዲስጥለት በወላጅ ጥያቄው ሲቀርብ መታወቂያው ሊሰጠው ይችላል፡፡

5.3 የኢትዮጵያ ተወላጅ ልጆች እድሜያቸው ለአካለ መጠን ሲደርስ በራሳቸው ጠያቂነት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ አሰጣጥ መስፈርትን ሲያሟሉ የተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

6 <u>ለኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅ የትዳር ጓደኛ ስለሚሰጥ የኢትዮጵያዊ ተወላጅነት መታወቂያ:-</u>

6.1 ለኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ያለው/ያላት የውጭ አገር ዜጋ ለትዳር ጓደኛው /ጓደኛዋ/ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እንዲሰጥለት/እንዲሰጥላት ከፈለገ/ች

6.1.1 ቢያንስ ሁለት (2) ዓመት የሆነው የጋብቻ ማስረጃ፣

6.1.2 የባል/የሚስት የኢትዮጵያዊ ዜግነት ማስረጃ ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ኮፒ፣

6.1.3 የትዳር ጓደኛው/ዋ በቅርብ ጊዜ የተነሳው/የተነሳችዉን/ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍና

6.1.4 ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ በማያያዝ

ከአገር ውጭ ሲሆን ለኢትዮጵያ ሚሲዮን በአገር ውስጥ ሲሆን ለኢሚግሬሽን ያቀርባል፡፡

6.2 መታወቂያው እንዲሰጥ የሚወሰነው ትዳሩ ጸንቶ ስለመኖሩ በማስረጃ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

7 <u>የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ጥያቄ በውጭ ሀገር በሚሲዮኖች እና በአገር ቤት በኢሚግሬሽን ስለሚቀርብበት ሁኔታ</u>

7. 1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ለማግኘት በውጭ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች ጥያቄው ሲቀርብ አመልካች በአካል ቀርቦ ወይም በሚሲዮኑ በሚዘረጋው የአሰራር ስርአት መሠረት የገቢውን የአገልግሎት ክፍያ እና ተፈላጊ ማስረጃዎችን በተመዘገበ የፖስታ መልዕክት በመላክ ጥያቄውን ያቀርባል፡፡ የፖስታ ወይም የመላላኪያ ክፍያዎች በአመልካቹ የሚሸፈኑ ይሆናል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
Ministry of Foreign Affairs
ሪከርድ ክፍል
Records Section

7. 2 ሚሲዮኑ በአንቀጽ 4 የተገለጹትን አስፈላጊ መረጃዎች በማሟላት ለኢሚግሬሽን ይልካል፡፡

7. 3 የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ተገቢ ማስረጃዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የተወላጅነት ማረጋገጫ ካርዱን አዘጋጅቶ ለሚሲዮኑ ይልካል፡፡ ሚሲዮኑም እንደ ሁኔታው አመቺነት ግለሰቡ በግንባር ሲቀርብ ወይም በፖስታ ቤት በመላክ ይሰጣል፡፡

7. 4 አመልካች በአገር ቤት የሚገኝ ሲሆን ጥያቄውን በቀጥታ ለኢሚግሬሽን በአካል በማቅረብ መስፈርቶችን አሟልቶ እና ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈፀም የትውልድ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርዱን ማግኘት ይችላል፡፡

8 <u>የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የአገልግሎት ክፍያ</u>

8.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የአገልግሎት ክፍያ በሚሲዮኖች ሲሆን ጥያቄው በቀረበበት ሀገር ገንዘብ በእለቱ ተመጣጣኝ የምንዛሬ ተመን ክፍያ ይፈጸማል፡፡

8.2 ጥያቄው የቀረበው በሀገር ቤት ሲሆን በዶላር ወይም በእለቱ የምንዛሬ ተመን መሠረት ክፍያው በብር ይፈጸማል፡፡

9 <u>የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ</u>

9. 1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ጥያቄ ለኢትዮጵያ ሚሲዮን ሲቀርብ ጥያቄው የቀረበለት ሚሲዮን ማመልከቻውን ከተገቢ ማስረጃዎች ጋር ተሟልተው በቀረበለት ቢበዛ በአስራ አምስት 15 የሥራ ቀናት ውስጥ ለኢሚግሬሽን ይልካል፡፡

9. 2 አመልካቹ መታወቂያው በአስቸኳይ እንዲዘጋጅለት ከፈለገ በራሱ ወጭ በፈጣን መልእክት እንዲላክለት ኤምባሲው መረጃውን በፖስታ አሽጐ በፈጣን መልዕክት ይላክለታል፡፡

9. 3 ኢሚግሬሽን ያልተሟሉ መረጃዎች ሲደርሱት ሚሲዮኑ መረጃዎችን አሟልቶ እንዲላክ ጥያቄው በደረሰው በአምስት 5 ቀናት ለሚሲዮኑ ምላሽ ይልካል፡፡

9. 4 ኢሚግሬሽንም ከሚሲዮኑ የተሟላ ማስረጃ ሲቀርብለት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያውን ከአስር /10/ የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሚሲዮኑ ይልካል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs

9. 5 በተመሣሣይ ሁኔታ ሚሲዮኑ የደረሰውን መታወቂያ ቢበዛ ከሰባት (7) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ለጠያቂው እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

9. 6 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ጥያቄ በቀጥታ ለኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ሲቀርብ ተገቢውን ማስረጃዎች ተሟልተው ከቀረቡ መታወቂያው በአምስት (5) የስራ ቀናት ውስጥ ይሰጣል፡፡

## ክፍል ሦስት

### 10 በአገር ቤት ለሚሰጥ አገልግሎት የኢትዮጵያ ተወላጅነት የመታወቂያ ካርድ መያዝ ስለማስፈለጉ

10. 1 የተሟላ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የተቀበለ ማንኛውም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ እና ሲወጣ እንዲሁም ማንኛውንም አገልግሎት ሲጠይቅ ዜግነት ያገኘበትን አገር የፀና ፓስፖርትና የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡

10. 2 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዘ የውጭ ሀገር ዜጋ ወደ አገር ቤት ሲገባ በዜግነት ፓስፖርቱ ላይ የመግቢያ የቀን ማህተም ተመቶበት እንዲገባ ይደረጋል፡፡

10. 3 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ የአገልግሎት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ለውጪ ሀገር ለኢትዮጵያ ሚሲዮን በሀገር ውስጥ ለኢሚግሬሽን በማመልከት መታደስ ይኖርበታል፡፡ የአገልግሎት ጊዜው ባበቃ መታወቂያ አገልግሎት አይሰጥም፡፡

### 11 የኢትዮጵያ ተወላጅ መታወቂያ ካርድ እድሳት

11.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እድሳት አገልግሎት የሚሰጠው ጥያቄው በ11.2 የተመለከቱትን በማሟላት ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሚሲዮን ወይም ለኢሚግሬሽን ሲቀርብ ነው፡፡

11.2 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እድሳት የሚፈጸመው

ሀ. ዜግነት ያገኘበት ሀገር የጸና የዜግነት ፓስፖርት ኮፒ

ለ. ቀደም ሲል የተሰጠው የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ኮፒ

ሐ. በአንቀጽ 8.1 መሠረት ክፍያ ሲፈጸም ነው፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs

11.3 በጋብቻ መሰረት የተሰጠ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እድሳት ጥያቄ ትዳሩ የጸና ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃና የኢትዮጵያ ተወላጅ በሆነው ባል/ሚስት የተፈረመ ማመልከቻ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 12 . የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ስለሚሰረዝበት ሁኔታ

12.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ በአዋጅ ቁጥር 270/94 አንቀፅ 14 መሠረት እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

12.2 ከላይ በአንቀጽ 12.1 መሰረት የኢትዮጵያ የተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እንዲሰረዝ በተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ሰጪ አካላት ወይንም በሌላ ወገን ለጋራ ቴክኒክ ኮሚቴው ሊቀርብ ይችላል፡፡

12.3 ጥያቄ አቅራቢው ወገን እንዲሰረዝ ጥያቄ ያቀረበበትን የኢትዮጵያ ተወላጅነት የመታወቂያ ካርድ ባለቤት ስም፣ አድራሻና ዜግነት እንዲሁም የተወላጅ መታወቂያው እንዲሰረዝ የሚያስችሉ አሳማኝ ምክንያቶች መኖራቸውን የሚገልጹ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

12.4 የኢትዮጵያ ተወላጅ በማግባቱ ምክንያት የተገኘ የተወላጅነት መታወቂያ እንዲሰረዝ የሚቀርብ ጥያቄ ትዳሩ በሕግ በፈረሰ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ለማሳወቅ ግዴታ በገባው ወይንም በማናቸውም ወገን ለጋራ ቴክኒክ ኮሚቴው ሊቀርብ ይችላል፡፡

12.5 ጥያቄ አቅራቢው ወገን እንዲሰረዝ ጥያቄ ያቀረበበትን የመታወቂያ ባለቤት ስም፣ አድራሻና ዜግነት እንዲሁም ጋብቻው በህግ የፈረሰ መሆኑን የሚያሳይ ደጋፊ ማስረጃ በማያያዝ በአገር ውስጥ ሲሆን ለኢሚግሬሽን፣ በውጭ አገር ሲሆን ለሚሲዮን ያቀርባል፡፡ ለሚሲዮን የቀረበ ጥያቄ ለጋራ የቴክኒክ ኮሚቴው ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር እንዲላክ ይደረጋል፡፡

## 13 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እርማት

13.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እርማት የሚደረገው የመታወቂያ ካርዱ ባለቤት የሚፈለገውን እርማት ጠቅሶ ሲያመለክትና እርማቱን ማድረግ ስለማስፈለጉ አሳማኝ ምክንያት ወይም ማስረጃ ሲቀርብ ነው፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs

13.2 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያው እንዲታረም ጥያቄ የቀረበው በመጀመሪያ መታወቂያ ከሰጠው አካል ውጭ ከሆነ እንደአስፈላጊነቱ ጥያቄው የቀረበለት የኢትዮጵያ ሚሲዮን ወይም ኢሚግሬሽን ምትክ የተወላጅ መታወቂያ ካርድ ከመስጠቱ በፊት መጀመሪያ የሰጠውን አካል በእርማቱ ጥያቄ ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

13.3 እርማቱ የስም ለውጥ ከሆነ ስልጣን ከተሠጠው ፍርድ ቤት የተሰጠ እና አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

13.4 መታወቂያ ካርዱ መያዝ ያለባቸውን መረጃዎች አስመልክቶ የሚደረግ እርማት ከአንድ ጊዜ በላይ መሆን አይችልም፡፡

## 14 የጠፋ ወይም የተበላሸ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ስለ መተካት

14.1 አመልካች ባለው የክፍያ ደንብ ለጠፋ ወይም ለተበላሸ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ሲተካ የሚጠይቀውን ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

14.2 ለጠፋ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ምትክ ሊሰጠው የሚችለው መታወቂያው ስለመጥፋቱ ከአካባቢው ፖሊስ ወይም አግባብ ካለው አካል በቂ የሆነ ማስረጃ ሲቀርብና የጠፋው የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ዝርዝር መረጃ ለኢሚግሬሽን ሲተላለፍ ነው፡፡

14.3 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እንዲተካ ጥያቄ የቀረበው በመጀመሪያ መታወቂያዉን ከሰጠው አካል ውጭ ከሆነ ጥያቄው የቀረበለት የኢትዮጵያ ሚስዮን ወይም ኢሚግሬሽን የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ መጀመሪያ የሰጠውን አካል እንደአስፈላጊነቱ መረጃና በጥያቄው ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

## 15 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ስለመመለስ

15.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዘ ሰው በአዋጅ ቁጥር 270/94 አንቀጽ 13 መሰረት በማናቸውም ጊዜና ምክንያት በፅሁፍ ማመልከቻ በማቅረብ መታወቂያ ካርዱን መመለስ ይችላል፡፡

15.2 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርዱን ለመመለስ ማመልከቻ ያቀረበ ማናቸውም የኢትዮጵያ ተወላጅ ፋይሉ ከመዘጋቱ በፊት በሱ ምክንያት

የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ የተሰጣቸው የቤተሰብ አባላትን መታወቂያ ካርድ መመለሱ ከተረጋገጠ በኋላ ብቻ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

### 16 የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴ አደረጃጀት

16.1 ከሚኒስቴሩና ከአገልግሎቱ የሚመደቡ ከሥራው ጋር አግባብነት ያላቸው አምስት (5) አባላት ያሉት የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴው ይመሰረታል፡፡

16.2 የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴው አባላት ከሥራው ጋር አግባብነት ያላቸው ሲሆኑ ኮሚቴው ከሚኒስቴሩ መ/ቤት በተመደበ ሰብሳቢ ይመራል፡፡ ቀሪዎቹ አባላት ሁለቱ ከሚኒስቴሩ የሚመደቡ ሲሆን ሁለቱ ከአገልግሎቱ የሚመደቡ ይሆናሉ፡፡

16.3 በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቆንስላ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተወካይ የጋራ ኮሚቴው ጸሀፊ በመሆን ያገለግላል፡፡

### 17 የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴው ተግባር

17.1 በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 መሠረት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ እንዲሰረዝ የሚቀርብ ጥያቄን ተቀብሎ በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩና ለአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ያቀርባል፡፡ ሲወሰንም የጋራ ኮሚቴው ሰብሳቢ የውሳኔ ሃሳቡን ለኢሚግሬሽን ያስተላልፋል፡፡

17.2 በጋብቻ ምክንያት የተገኘ መታወቂያ ጋብቻው በሕግ በመፍረሱ ምክንያት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ እንዲሰረዝ ጥያቄ ሲቀርብ የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴው ተቀብሎ በመመርመር የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስቴሩና ለአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ያቀርባል፣ ሲወሰንም የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴው ሰብሳቢ ውሳኔውን ለኢሚግሬሽን ያስተላልፋል፡፡

17.3 ከኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን በተመለከተ የውሳኔ ኃሳብ ለበላይ አመራር ያቀርባል፡፡

17.4 መመሪያው በሚሲዮኖችና በኢሚግሬሽን በትክክል በሥራ ላይ መዋሉን ክትትል ያደርጋል፣

### 18 የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴው አሠራር

የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴው ሥራውን የሚመራበት የአሠራር ሥርአት ያዘጋጃል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs

## 19 የበላይ አመራሩ ተግባርና ኃላፊነት

19.1 የበላይ አመራሩ የኢትዮጵያ ተወላጅነት አዋጁ እንዲተገበር ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፣

19.2 ለጋራ የቴክኒክ ኮሚቴው ተገቢውን አመራር በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል፣

19.3 የኢትዮጵያ ተወላጅነት አዋጅና ደንብ እንደተጨባጭ ሁኔታው የሚሻሻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

19.4 የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴ የሚያቀርበውን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ያፀድቃል፣ ውሳኔው ተግባራዊ መሆኑንም ይከታተላል፣

19.5 የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴ የሚያቀርበውን የውሳኔ ሃሳብ በቀረበለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፣

19.6 የበላይ አመራሩ በሚያካሂደው የጋራ ስብሰባ የጋራ ቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ ፀሐፊ ሆኖ ያገለገለግላል፣

19.7 ሚኒስትሩ ወይም የአገልግሎቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ለዚሁ ሥራ ለሚኒስትር ዴኤታዎቹ ወይም ለምክትል ሥራ አስኪያጆቹ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## 20 የተሻሩ መመሪያዎች

ከዚህ በፊት ግንቦት 1/1994 የወጣው የማስፈጸሚያ መመሪያ በዚህ የማሻሻያ መመሪያ ተተክቷል።

## 21 መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 26 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Foreign Affairs

ዶ/ር ቴድሮስ አድሐኖም ገብረየሱስ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

ፎቶ
Photo

የፎርም ቁጥር ______________

Ref.No ____________________________

**ቅጽ 1**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**

**የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ መጠየቂያ ፎርም**

**Application form for the grant/renewal Persons of Ethiopian Origin Identification Card**

1. የአመልካች ሙሉ ስም(ከነአያት)
   Full Name ________________________________________________
2. ሌሎች የሚጠራባቸው ስሞች ካሉ
   Other Nick Name ____________________________________
3. ፆታ
   Sex __________
4. የትውልድ ዘመን ወር ቀን ዓ.ም-
   Date of Birth ____________ Month _________ Day _______ Year _________
5. የተወለደበት ቦታ
   Place of Birth ____________________________________

5.1. በውጭ ሀገር ከሆነ
Out of Ethiopia ______________
ሀገር
Country ______________ የመንገድ ስምና ቁጥር Street Name & No. ____________________________________
ከተማ
City _____________________

5.2. በሀገር ውስጥ ከሆነ
In Ethiopia
ክልል ___________________________ ከተማ/ክፍል ከተማ
Region/Kifle Hager________________ City________________
ወረዳ ቀበሌ
Woreda ____________________ Kebele _______________

5.3. በሀገር ቤት የወላጅ/የቅርብ ቤተሰብ አድራሻ
ክልል _____________________ ከተማ/ክፍል ከተማ/ዞን ___________________
Region/____________________ Sub-City/Zone________________
ወረዳ __________________________________ ቀበሌ
Woreda ____________________ Kebele _______________

5.4. ሀገር ቤት የተማረበት ት/ቤት ስም ________________________________________
Name of school attended

5.5. በሀገር ቤት የሠራባቸው መ/ቤቶች ስም ________________________________________
Name of organizations the applicant served at home

5.6. ተጨማሪ ማስረጃዎች ( መንጃ ፍቃድ ፣ የትምህርት ማስረጃ፣ ሌሎች)
Additional documents (driving license, educational testimonial & others)

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs

6. **ዜግነት**
Nationality
6.1. **የቀድሞው**
Former 1.______________ 2.______________ 3.________________
6.2. **የአሁኑ**
Present 1.______________ 2.______________ 3.________________
6.3. **የትውልድ ዘር**
Ethnic Origin ___________________________

7. **ዜግነት ከተሰጠው ሀገር የተሰጠ ፓስፖርት**
Valid Passport issued by the country of nationality to a person of Ethiopian origin
7.1 **ፓስፖርት**
Passport No.________________
7.2 **የተሰጠበት ቦታ**
Place of Issuance _____________
7.3 **የተሰጠበት ቀን**
Date of Issue _______________
7.4 **የሰጠው አካል**
Issuing Authority _________________________
7.5 **የሚጸናበት ጊዜ**
Date of Expiry _____________________

8. **የአመልካቹ የሚስት ወይም የባል ሙሉ ስም**
Applicant's spouse full Name ______________________________
**የትውልድ ቀን ወር ዓመት**
Date of Birth__________________________
**የመኖሪያ አድራሻ**
Address __________________
**ዜግነት**
Nationality____________________

9. **ድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች**

| ተራ ቁጥር No. | የልጅ /የጥገኛ ስም Name of the Child/Dependent | የፓስፖርት ቁጥር Passport No. | ምርመራ Remark |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

10. **የውጭ ዜግነት ከያዘ በኋላ የሠራባቸው ቦታዎች እና በአሁኑ ወቅት ያለው የትምህርት ደረጃና ሙያ**
Occupations since acquiring foreign nationality and present educational level and profession.
10.1. **የአሁን ሥራ**
Present Occupation _________________,________________,______________,___________
10.2.**ቀደም ሲል የሰራባቸው ቦታዎች**_____________________
Previous Occupations_________________,________________,_________________,___________
10.3.የትምህርት ደረጃ (የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለተኛ ዲግሪ፣ ሶስተኛ ዲግሪ፣ ሌላ)
Educacional level 1st Degree, 2nd Degree, 3rd Degree and others
10.4 Others _________________________
(Profession) ______________________

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs

10.5 የመኖሪያ አድራሻ

Present Address

አገር ከተማ የመንገድ ስምና ቁጥር

Country______________ City_____________ Street Name & No___________________

ፖ.ሣ.ቁ ስልክ ቁጥር

P.O.Box ____________________ Telephone No. _____________________

ፋክስ ቁጥር ________________ ኢ-ሜል _______________.

Fax ____________________________ e-mail ____________.

**11.** የኢትዮጵያን ተወላጅነትን የሚያስረዱ ማስረጃዎች ዝርዝር ቅጂዎች ይያያዙ።

(Please attach evidences that prove Ethiopian origin)

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**12.** በዚህ ቅጽ የሞላኋቸው መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን እያረጋገጥኩ፣ ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ባቀርብ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ እንደምሆን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ ::

I hereby declare that the details that I provided above are true.

__________________________ __________________________

ቀን/Date ፊርማ/Signature

**13.** ቅጹን ያረጋገጠው ሃላፊ

Approved By :-

ሥም___________________________________

Name ________________________________

ፊርማ ________________________________

Signature _____________________________

ቀን _________________________________

Date ________________________________

<u>ለቢሮ ሥራ ብቻ(FOR OFFICE USE ONLY)</u>

የመታወቂያ ካርድ ቁጥር-----------------

ቀን-----------------------------------------

የሰጠው ሃላፊ ----------------------

የተከፈለው ገንዘብ-------------------------

የደረሰኝ ቁጥር ---------------------------

መታወቂያ ያገኘበት ሁኔታ ------------



ፎቶ
Photo

የፎርም ቁጥር ______________

Ref.No ----------------------------

**ቅጽ 2**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**

**የኢትዮጵያ ተወላጅ ባል ወይም ሚስት ለሆኑ የሌላ ሀገር ዜጎች መታወቂያ ካርድ መጠየቂያ ፎርም**
**Application form for the grant/renewal Persons of Ethiopian Origin Identification Card**

እኔ አመልካች አቶ /ወ/ሮ______________________ዜግነት_____________ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ቁጥር_____________ የተሰጠበት ቀን________________የተሰጠበት ቦታ__________ የሆነ መታወቂያ ካርድ /ኢትዮጵያዊ ፓስፖርት/ የቀበሌ መታወቂያ ቁጥር__________________ የተሰጠበት ቀን________________የተሰጠበት ቦታ______________ የሆነ የያዝኩ በዛሬው ______________ቀን_______________ዓ.ም. ለባለቤቴ _______________________ለኢትዮጵያ ተወላጅ ባል ወይም ሚስት ለሆኑ የውጭ ሀገር ዜጎች መታወቂያ ካርድ እንዲሰጥ እያመለከትኩ ሲፈቀድም ትዳሩ ፀንቶ ባይቆይ በሕግ በፈረሰ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቤ የማሳወቅ መሆኔን በፍርማዬ አረጋግጣለሁ::

ስም______________________
ፍርማ___________________

I,Mr______________________ the undersigned applicant, national of_______________,holder of the ID card of person of Ethiopian origin/Ethiopian passport /kebele identity card No,_____________issued on________________date of 20___applay for my spouse______________________ to be issued for the ID of the spouse of the Ethiopian origin and commit myself to inform the issuing authority within one month whenever there is a legal divorse/separation.

Name______________________________
Signature____________________________

1.የአመልካች ሙሉ ስም(ከነአያት)

Full Name ______________________________________________

2.ሌሎች የሚጠራባቸው ስሞች

Other Nick Name__________________________________

3.ፆታ

Sex __________

4.የትውልድ ዘመን ወር ቀን ዓ.ም-

Date of Birth ____________Month _________ Day _______Year _________

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs

**5.የተወለደበት ቦታ**

Place of Birth ______________________________

**5.1.በውጭ ሀገር ከሆነ**

Out of Ethiopia____________

**ሀገር**

Country ____________ Street Name & No. ______________________________

**የመንገድ ስምና ቁጥር**

**ከተማ**

City __________________

**5.2.በሀገር ውስጥ ከሆነ**

In Ethiopia

**ክልል**

Region/Kifle Hager_______________

**ከተማ/ክፍል ከተማ**

City______________

**ወረዳ**

Woreda _________________

**ቀበሌ**

Kebele _____________

**6.ዜግነት**

Nationality

**6.1.የቀድሞው**

Former 1.____________ 2.____________ 3.______________

**6.2.የአሁኑ**

Present 1.____________ 2.____________ 3.______________

**6.3.የትውልድ ዘር**

Nationality by Birth_______________________

**7.ዜግነት ከተሰጠው ሀገር የተሰጠ ፓስፖርት**

Valid Passport issued by the country of nationality to a person of Ethiopian origin

7.1 **ፓስፖርት**

Passport No.______________

7.2 **የተሰጠበት ቦታ**

Place of Issuance ___________

7.3 **የተሰጠበት ቀን**

Date of Issue _____________

7.6 **የሰጠው አካል**

Issuing Authority ______________________

7.7 **የሚጸናበት ጊዜ**

Date of Expiry __________________

**8. የአመልካቹ የሚስት ወይም የባል ሙሉ ስም**

Applicant's spouse full Name __________________________

**የትውልድ ቀን ወር ዓመት**

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs

Date of Birth________________________

የመኖሪያ አድራሻ

Address ________________

ዜግነት

Nationality__________________

9. እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች

| ተራ ቁጥር No. | የልጅ /የጥገኛ ስም Name of the Child/Dependent | የፓስፖርት ቁጥር Passport No. | ምርመራ Remark |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

10.የውጭ ዜግነት ከያዘ በኋላ የሠራባቸው ቦታዎች

Occupations since acquiring foreign nationality

10.1. የአሁን ሥራ

Present Occupation _______________,_______________,_______________

10.2.ቀደም ሲል የሰራባቸው ቦታዎች__________,_______________,_______________

Previous OccupationS

10.3. የመኖሪያ አድራሻ

Present Address

አገር ከተማ የመንገድ ስምና ቁጥር

Country____________ City____________ Street Name & No________________

ፖ.ሣ.ቁ ስልክ ቁጥር

P.O.Box ________________ Telephone No. ________________

11.የኢትዮጵያን ተወላጅነት የሚያስረዱ ማስረጃዎች ዝርዝር ቅጂዎች ይያያዙ(Please attach evidences that prove Ethiopian origin)

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

12.በዚህ ቅጽ የሞላኋቸው መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::

I hereby declare that the details that I provided above are true.

________________ ________________

ቀን/Date ፊርማ/Signature

13. ቅጹን ያረጋገጠው ሃላፊ

Approved By:-

ሥም__________________________

Name __________________________

ፊርማ __________________________

Signature __________________________

ቀን __________________________

Date __________________________

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

ሪከርድ ክፍል

Records Section

Ministry of Foreign Affairs

ለቢሮ ሥራ ብቻ(FOR OFFICE USE ONLY)

የመታወቂያ ካርድ ቁጥር-----------------

ቀን---------------------------------------

የሰጠው ባለሥልጣን----------------------

የተከፈለው ገንዘብ-------------------------

የደረሰኝ ቁጥር -------------------------

መታወቂያ ያገኘበት ሁኔታ ------------

ፎቶ
Photo

የፎርም ቁጥር ______________

Ref.No --------------------------

**ቅጽ 3**
**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**Ministry of Foreign Affairs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**

**በልዩ ሁኔታ ለውጭ አገር ዜጎች የሚሰጥ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ መጠየቂያ ፎርም**
**Application form for the grant/renewal of foreign nationals residing in Ethiopia of Ethiopian Origin Identification Card Foreign nationals on special condition**

1. የአመልካች ሙሉ ስም (ከነአያት)
   Full Name ______________________________________
2. ሌሎች የሚጠራባቸው ስሞች ካሉ
   Other Nick Name ______________________________
3. ፆታ
   Sex __________
4. የትውልድ ዘመን ወር ቀን ዓ.ም-
   Date of Birth ____________Month _________ Day _______Year _________
5. የተወለደበት ቦታ
   Place of Birth ______________________
6. ዜግነት___________________
   Nationality__________________

6.1 ፓስፖርት
   Passport No.________________

6.2 የተሰጠበት ቦታ
   Place of Issuance _____________

6.3 የተሰጠበት ቀን
   Date of Issue _______________

6.4 የሰጠው አካል
   Issuing Authority __________________________

6.5 የሚጸናበት ጊዜ
   Date of Expiry ______________________

6.6 በኢትዮጵያ የመኖሪያ አድራሻ
   Present Address
   አገር ከተማ/ክልል
   Country______________ City_____________ ክ/ከተማ___________ወረዳ__________-
   ፓ.ሣ.ቁ ስልክ ቁጥር
   P.O.Box _____________________ Telephone No. _____________________

7. የአመልካቹ የሚስት ወይም የባል ሙሉ ስም (የጋብቻው ማስረጃ ይያያዝ)
   Applicant's spouse full Name (attach mariage certificate) ______________________________
   የትውልድ ቀን ወር ዓመት
   Date of Birth___________________________
   የመኖሪያ አድራሻ
   Address ___________________
   ዜግነት
   Nationality_____________________
   ጋብቻው የተፈፀመበት ቀን_________________
   Date of mariage______________________

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር * Ministry of Foreign Affairs *
ሪከርድ ክፍል
Records Section

8. እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች
Children below the age of 18

| ተራ ቁጥር No. | የልጅ Name of the Child | የፖስፖርት ቁጥር Passport No. | ምርመራ Remark |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

9. በኢትዮጵያ ውስጥ ያገለገለባቸው ተቋማት______________________________
Institutions in which the applicant served in Ethiopia______________________________

10. የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም በማስከበር ያበረከቷቸው በአራአያነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ሥራዎች ይገለፁ (በማስረጃ ይደገፍ)______________________________
______________________________
Examplary ativities undertaken by the applicant that would serve the national interest of Ethiopia (Support by evidence)______________________________
______________________________

11. በዚህ ቅጽ የሞላኋቸው መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ::
I hereby declare that the details that I provided above are true.

______________ ቀን/Date ______________ ፊርማ/Signature

12. ቅጹን ያረጋገጠው ሃላፊ
Approved By:-
ሥም______________________________
Name ______________________________
ፊርማ ______________________________
Signature ______________________________
ቀን ______________________________
Date ______________________________

**ለቢሮ ሥራ ብቻ(FOR OFFICE USE ONLY)**

የመታወቂያ ካርድ ቁጥር------------------
ቀን------------------------------------
የሰጠው ባለሥልጣን----------------------
የተከፈለው ገንዘብ-----------------------
የደረሰኝ ቁጥር -------------------------
መታወቂያ ያገኙበት ሁኔታ -------------

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
ሪከርድ ክፍል
Records Section
Ministry of Foreign Affairs